# ***<u>አድዋ ተናገር !!</u>***

*አሥራደው (ከፈረንሳይ)*

*« የአድዋ ድል ለደቡቡ ምኑ ነው?!» ቢሉን፤ እኛም አድዋን ተናገር?! አልነው፤*
*« ሰንደቅ ዓላማችንን ጨርቅ እያሉ ቢሳለቁበት » በአያቶቻችን ደም የቀላ የድል ዓርማችንን የሚያጎድፉ ሁሉ የታሪክ ተጠያቂ ይሆናሉ አልናቸው::*




*ኧረ ለመሆኑ ማነው የሞተልህ ?*
*ማንስ አስደፍሮ ማንስ ዘብ ቆመልህ ?*
*ሥጋውን አጥንቱን ማን ከሰከሰልህ ?*
*ሞቱን ባንተ ሸሮ ድል አጎናጸፈህ ?!*
*በሕይወቴ እያለሁ ጠላት አይደፍርህም ፤*
*ጣልያን ባንተ ጉያ አይውልም አያድርም ፤*
*ፋሺስት ባንተ መንደር አይምነሸነሽም ፤*
*ብሎ የተመመው ላንተ ሊሞትልህ ፤*
*ላንተ የቆሰለው ላንተ የደማልህ፤*
*አርነት ያወጀው ድል ያጎናጸፈህ፤*
*ኧረ ለመሆኑ ትግሬ ብቻ ነበር ?*
*ወይንስ **ጦብያ** መላው ድፍን አገር ?!*

አድዋ ተናገር!!
ቃልኪዳን አትፋቅ ማተብ አትበጥስ ፤
በደም የተጻፈ ታሪክ አትከልስ ፤
እረ ለመሆኑ ማነው የሞተልህ ?!
ማነው የቆሰለው ማነው የደማልህ ?
አጥንቱን ከስክሶ ድል ያጎናጸፈህ ?!

ቼ ! ብሎ የተመው ነጋሪት የመታው ፤
እንቢልታውን ነፍቶ ፎክሮ የወጣው ፤
ጎራዴውን መዞ ጠሩን የሰበቀው ፤
አንተ እንዳትደፈር ቃልኪዳን የገባው፤
ላንተ የሞተልህ ላንተ የተሰዋው ፤
መላው ኢትዮጵያዊ ድፍን አገሩ ነው ?
ወይስ አንድ ጎሳ ብቻውን ትግሬ ነው ??

አድዋ ተናገር !
ቃልኪዳን አትፋቅ ማተብ አትበጥስ ፤
በደም የተጻፈ ታሪክ አትከልስ ፤
እረ ለመሆኑ ማነው የሞተልህ ?!
ማነው የቆሰለው ማነው የደማልህ ?
አጥንቱን ከስክሶ ድል ያጎናጸፈህ ?!

አድዋ ተናገር ምንድነው ዝምታው ?!
ትግሬ ብቻ ነበር ላንተ ሲል የሞተው ?
ድንበር ያስከበረው ደሙን ያፈሰሰው ?
ወይስ መላው አገር ?!
ሲዳሞና ሐረር ፤
ወለጋና ጎንደር ፤
ሸዋና ወሎየው ፤
አርሲው ጎጃሜው፤
ኢሉባቡር ከፋው ፤
ባሌ ጋሞገፋው ፤
ኤርትራና ትግሬው ፤
አልነበረም እንዴ ላንተ ሲል የሞተው ?!
በዘር ሳይታጠር ሃይማኖት ሳይፈታው ፤
ጥቅም ሳይደልለው ድህነት ሳይረታው ::

እምቢኝ ላገር ብሎ እምቢኝ ላንተ ብሎ ፤
ሚስትና ልጆቹን እርግፍ አርጎ ጥሎ ፤
እርሻው አይታረስ አረም ይብላው ብሎ ፤

አረም እንዳይበቅል ባድዋ ተራራ ፤
በጎራዴው አርሶ ጥይቱን የዘራ ፤
ጭንቅላት የቀላው በጩቤ በካራ ፤
ድሉን ያደመቀው በጀግና ፋከራ ፤
ትግሬ ብቻ ነበር ?
ወይስ መላው አገር ?
አድዋ ተናገር !
በማተብህ ጽና ለሕሊናህ እደር ::

ከሰሜን ከደቡብ ርቀት ሳይገድበው ፤
ከምዕራብ ከምሥራቅ ፀሐዩ ሳይገታው ፤
ሆ ! ብሎ የወጣው ላንተ የሞተልህ ፤
ሞቱን ባንተ ሸሮ ድል ያጎናጸፈህ ፤
ኧረ ለመሆኑ ትግሬ ብቻ ነበር ?
ወይንስ **ጣብያ** መላው ድፍን አገር ??
አድዋ ተናገር !
ቃል ኪዳን አትርሳ ማተብ አትበጥስ ፤
በደም የተጻፈ ታሪክ አትከልስ ::

ዛሬ ዘመን ከፍቶ አገር ተበትኖ ፤
በዘር በሃይማኖት ጎሳ ተሸንሽኖ ፤
አገር እበት ወልዳ ትል ደሟን ሲጠባ ፤
በባንዳ ታጅቦ ጠላት ቤት ሲገባ ፤
አድዋ የኛ ነው ! ላንተ ምንህም ነው !
ይሉን ጀምረዋል ጥንቱን እያወቅነው ፤
አድዋ ያለ እናቱ፤
አድዋ ያለ ኢትዮጵያ የሙት ልጅ ባዳ ነው ::

አድዋ ተናገር !
በቃል ኪዳን ጽና ለማተብህ እደር ፤
በደም የተጻፈ ታሪክ አትሸርሽር ፤
ላንተ የሞተልህ ትግሬ ብቻ ነበር ?!
ወይንስ **ጣብያ** መላው ድፍን አገር ??

አንድ ቀን

በዘር፤ በሃይማኖት፤ በጎሳ፤ በጎጥ፤ ሳይከፋፈሉ ለኢትዮጵያ ነፃነትና
ለሰንደቅ ዓላማችን መከበር ሲሉ በአድዋና በሌሎች የጦር ሜዳዎች
ለወደቁ የኢትዮጵያ ጀግኖች በሙሉ መታሰቢያ ትሁንልኝ ::